# በኢትዮጵያ በ ሃብታምና በድሃ መካከል እየሰፋ የሚሄደው  ልዩነት ለምን ያሳስበናል?

**ሰለሞን ገ/ስ**



**እንደ ፈረንጆቹ አቆጣጠር በ 2012  “እያደገ እየሄደ ያለዉ  የሃብት ልዩነት በኢትዮጵያ“ በሚ ል ር እስ አቡጊዳንና አባይ ሚዲያን በመሳሰሉ ድረ ገጾች ላይ አንድ ጽሁፍ አዉጥቼ ነበር። በጽሁፉ እየሰፋ የሄደዉን የሃብት ልዩነት ለማሳየት ብሞክርም፤ለምን ይህ ነዉር እንደሆና ለምንስ ሊያሳስበን እንደሚ ገባ አላወሳሁም ነበር። በዚህ ጽሁፍ ለእነዚህ መሰረታዊ ጥያቄዎች መልስ ለመስጠት እሞክራለሁ።**

**የ60ዎቹ ትዉልድ ወጣቶች ህብረተሰባዊ እኩልነትን የሚያምንና የሚያስተምር ርእዮተ አለም (ማርክሲዝም ሌኒኒዝም) ተከታዮች ስለነበሩ ለእነሱ  ለእኩልነት መታገል ባእድ ሃሳብ አልነበረም። በተጨማሪም ባገራችን በዚያን ወቅት መሬትን፤ የከተማ ቤቶችንና ፋብሪካዎችን የመሳሰሉ ትርፍ አስገኚ ንብረቶች በጥቂቶች የተያዙበት፤ ብዙሃኑ ደግሞ ጭሰኛ፤ተከራይ ወይም ሰራተኛ የሆነበት ስርአት ስለነበር፤ የተፈጠረዉን ልዩነት ለማስተካከል መሞከሩ ተፈጥሯዊ ነበር። የዛሬዉ  ትዉልድ እንደዚያ ዘመን ትዉልድ እየሰፋ የሚሄደዉን የሃብት ልዩነት ለማጥበብ ማጠየቂያ ር እዮተ አለም  የለዉም። በርግጥ ታላቆቹ የኢትዮጵያ ሃይማኖቶች ለድሆች ርህራሄ ማሳየት መሰረታዊ ትምህርታቸዉ ቢሆንም፤ ሃይማኖት ብቻ በራሱ በቀጣይነት ልዩነቱን ለማጥበብ ለሚደረግ ትግል በቂ ነዳጅ መሆን አይቻለዉም። በዚህ ላይ ደግሞ ግሎባላይዜሽን የተባለዉ አለምን በቴክኖሎጂ  ያቀራረበ ስልተምርት የሃብታም ይበልጥ ሃብታም መሆን “ተፈጥሯዊ“ ማስመሰል ስልቱ ስለሆነ ህብረተሰቡ ዉስጥ ወደኋላና ወደታች የቀሩት እንዲረሱና አጀንዳ እንዳይሆኑ የበኩሉን አስተዋጽኦ ያደርጋል። ዛሬ በተለይም በዉጭ ሃገሮች  ሰፊ  ትምህርት ያገኙ ወጣት ኢትዮጵያዉያን ወደሃገራቸዉ ኢትዮጵያ ተመልሰዉ በ አለም አቀፍ ኮርፖሬሽኖች ተቀጥረዉ “ብዙ ገንዘብ መስራት“ የሚለዉ መፈክራቸዉ ነዉር ባይሆንም፤ “ብዙ ገንዘብ ከመስራት“ አኳያ፤ ከኢኮኖሚዉ ዳቦ ድርሻቸዉን ያላገኙትን ኢትዮጵያዉያንም ማስታወስና ኑሯቸዉ እንዲሻሻል የመርዳትም ሃላፊነት ጭምር እንዳለባቸዉ ማስታወስ ያስፈልጋል።**

**ይህ ደግሞ ተገቢ የሚሆነዉ የፍትህ ጥያቄ ስለሆነ ነዉ።**

፩

ፈላስፎችና ታላላቅ የሃይማኖት መሪዎች   ከጥንት ጀምሮ ህብረተሰብ በፍትህ ላይ የተመሰረተ እንዲሆንና ሰዉ ደግሞ ምግባረ ጥሩ  ለመሆን እንዲጥር አስተምረዋል። አሪስቶትልና ፕላቶ የተባሉ የታወቁ የግሪክ ፈላስፋዎች ከበጎ ምግባሮች ሁሉ ፍትህ ቀዳማይ እንደሆነች አስተምረዋል። በተለይ የ ኢንዱስትሪ አብዮት የተባለዉ ዘመናዊ ስልጣኔ በአዉሮጳ ከገባ በኋላ፤ የ ሃብት ክምችት በመጨመሩ፤ በደሃና በሃብታም መካከል ያለዉ ልዩነት ቀስ በቀስ እየጨመረ ለመሄድ በቅቷል። ከ 15ኛዉ ክፍለዘመን ጀምሮ በሚታወቀዉ የሳይንስ፤ የስነ ጥበብ፤ የምርምርና በጠቅላላዉ "ዘመነ ብርሃን" -ኢንላይትመንት - በተባለዉ ወቅት የተነሱ ፈላስፋዎች አብዛኛዉን ምርምራቸዉንና ጥናታቸዉን ያደረጉት በፍትህና በእኩልነት ጥያቄዎች ዙሪያ ነበር። ይህ ደግሞ ራሱ "ሰዉ ማለት ምን ማለት ነዉ? ምንስ መብቶች አሉት?" ከሚሉት ጥያቄዎች ጋር በጥብቅ ሊተሳሰር ችሏል።

ይህ ማለት አንድ ሰዉ ጥሮ ግሮ፤ ወይም ከመሳፍንትና ከልኡላን ተወልዶ ያፈራዉንና የወረሰዉን  ንብረትና ሃብት ባንድ በኩል እንደወረደ መቀበል ብቻ ሳይሆን፤ ለምን ይህ ሰዉ ሌሎች በአምሳሉ የተፈጠሩትን ለማዘዝና ለመቅጠር ቻለ? እነዚህስ ለምን ድሃ ሆኑ? ባንድ ህብረተሰብ እየኖሩ ይህ አይን ያወጣ የሃብት ልዩነት ትክክል ነዉ ወይ? ብሎ ጭንቅላትን ማሰራትና መፈተሽ ማለት ነዉ። ከነዚህ የዘመነ ብርሃን ፈላስፎች መካከል ወደ መጨረሻዉ የተነሳዉ ጀርመናዊዉ አማኑኤል ካንት የተባለዉ የሰዉን ልጅ መብትና ክብር፤ ድሃ ይሁን ሃብታም ሳይለይ በሰዉነቱ ብቻ ሃይማኖትንም ሳያጣቅስ፤ ሰዉ በመሆኑ ብቻ ክብርና ዋጋ እንዳለዉ በምንም ሚዛንና ሁኔታ እንደማይለወጥና የማይገሰስ መብት ባለቤት እንደሆነ በማያሻማ ሁኔታ አስቀመጠዉ።

ይህ አስተሳሰብ ባብዛኛዉ አገሮች ተቀባይነት አግኝቶ እንዲያዉም በአለም አቀፍ ማህበሮች ዘንድ ለምሳሌ እንደተባበሩት መንግስታት አይነት ድርጅቶች ለሰዉ ልጅ ሰብአዊና ዴሞክራሲያዊ መብቶች ድንጋጌ የማይናወጽ መሰረት ሊሆን በቅቷል። የአማኑኤል  ካንት የሰዉ ልጅ ክብርነት ፍልስፍና በዘመኑ ተፎካካሪ የነበሩትን፤ ለምሳሌ "አብዛኛዉ ሰዉ ደስተኛ እስከሆነና ትርፍ እስካገኘ ድረስ የሚወሰዱ ርምጃዎች ትክክል ናቸዉ" የሚለዉን ዩቲሊቴርያኒዝም የተባለዉን በብዙሃንና በህዳጣን ላይ የተመሰረተዉን ፍልስፍና ፉርሽ አድርጓል። በኋላም በተለይ በሃየኛዉ ክፍለዘመን አጋማሽ ላይ ለሚሊየኖች ህይወት መጥፋት የሆኑትን እንደ ስታሊኒዝም የመሳሰሉትን እምነቶች፤ ማለትም "የመጨረሻዉ ዉጤት መጀመሪያ የተወሰደዉን የሃይል ርምጃ ያስተሰርየዋል" የሚለዉን ስህተተኝነት፤ የሰዉ ልጅ ክቡርነት ለምንም ድርድር የማይቀርብና በተምኔት  ወደኋላ ይገኛል በሚባል ምድራዊም ሆነ ሰማያዊ ጸጋ እንደማይተካ ካንት በትክክል አስረግጧል።

አማኑኤል ካንት ከሞተ ከ 200 አመታት በኋላ የሰዉ ልጅ እኩልነት ጉዳይና የፍትህ ጥያቄ፤ ከአዉሮጳ የባህር ዳርቻ ተሻግሮ ወደ አሜሪካ ፈላስፎች መጥቷል። በተለይም በሃርቫርድ ዩኒቨርሲቲ የሚያስተምሩ ወይም የሚመራመሩ ፈላስፎችና ጠበብቶች እኩልነትንና ፍትህን በሚመለከት በርካታ ጽሁፎችናን መጽሃፍትን አበርክተዋል። ከነዚህ መካከል ጆን ራዉልስ፤ሮበርት ኖዚክ፤ማይክል ሰንደል፤ አማርትያ ሴንና ሪቻርድ ድዎርኪን ስመ ጥሩዎች ናቸዉ። ባንድ ወቅት ሃርቫርድ ያስተምር የነበረዉ ጥቁር አሜሪካዊዉ ኮርኔል ወስትም እዚሁ የስም ዝርዝር ዉስጥ መካተት ይኖርበታል። ምንም እንኳ አንዳንድ አቻዎቹ በፈላስፋነት ሊቀበሉት ፈቃደኛ ባይሆኑም፤ ፍልስፍናንና የክርስቲያን እምነትን በማቆራኘት ያበረከታቸዉ ጽሁፎችና ከሌሎች ተራማጆች በመጠቀ ሁኔታም ለድሆች መታገሉና በ አሜሪካ ዉስጥ በቀለም ላይ ተመስርቶ ከፉኛ የሚያሳዝነዉን ጥቁሮችና ሌሎች ህዳጣን በእስር ቤት መታጎራቸዉን ከሚቃወሙት ዉስጥ ቀንደኛ ነዉ።

ልክ እንደ ፈላስፎቹም በተለይ በሃብታምና በደሃ እየሰፋ የሚሄደዉን በምእራቡም አለም ጭምር የሚታየዉን ክስተት በተመለከተ አንዳንድ የቁጠባ ሃብት አጥኝዎችም ( ኢኮኖሚስቶችም) በጉዳዩ በሰፊዉ ይጽፉበታል። ከነዚህም ለናሙና ያህል ስሞች ለመጥቀስ ጆሴፍ ስቲግሊትዝ፤ፈረንሳዩ ቶማስ ፒኬቲ (በ2014 "ወረት በ 21ኛዉ ክፍለዘመን" በሚል ርእስ የጻፈዉ ከፍተኛ ተነባቢነትን ካገኙ መጽሃፍት ምድብ ነበር)፤ አማኑኤል ሴይዝና ጂ.. ዘክማንን ይገኛሉ። አማርትያ ሴን ልክ ካርል ማርክስ ያደርግ እንደነበረዉ ፍልስፍናና ኢኮኖሚክስን አዳብሎ በሁለቱም በሰፊዉ የሚጽፍ ምሁር ነዉ።

ከፊታችን የተደቀነዉን ጥያቄ ማይክል ሰንደል እንደሚከተለዉ አስቀምጦታል። "አንድ አገር ወይም ህብረተሰብ በፍትህ ላይ የተመሰረተ ነዉን? ብለን ስንጠይቅ የምንጠይቀው እንዴት ነዉ ያ አገር ገቢና ንብረትን ለዜጎቹ የሚያከፋፍለዉ? ግዴታዎችንና መብቶችንስ? ስልጣንና እድሎችን? ሽልማቶችንና ሃላፊነቶችን? ማለታችን ነዉ ይለናል። በፍልስፍና ተያያዡ ጥያቄም በምን ሚዛን ነዉ እነዚህ ክፍፍሎች የሚደረጉት የሚለዉ ነዉ። ("ፍትህ፤

መደረግ ያለበት ትክክለኛዉ ነገር ምንድን ነዉ" 2009)

ከላይ የተጠቀሱት ፈላስፎች ሁሉ ይህን ጥያቄ ለመመለስ ሞክረዋል። ሁለቱ ማለትም ጆን ራዉልስና ሪቻርድ ድዎርኪን መላምታዊ ሁነቶችን በመጠቀም ሰዉ ኢጋጣሚዉን ሲያገኝ ፍትህን የሚያነግስ ስር አት እንደሚመርጥ ለማሳየት ሞክረዋል። ራዉልስ ያለ አንዳች እዉቀት አምሮአችንን ሸፍነን (veil of ignorance) ማለትም፤ መደባችንን፤ጾታችንን፤ ሃብታችንን ወዘተ ሳናዉቅ ህብረተሰብ እንዴት ይደራጅ ተብለን ብንጠየቅ የምንመልሰዉ መልስ ሁለት መሰረታዊ የፍትህ ዋልታዎችን ያስመርጠናል ይላል። እነዚህም አንደኛ ህብረተሰቡ በጸና መሰረት ላይ መቆሙን የሚያረጋግጥ ዛሬ በ ምእራብ አገሮች እንደምናየዉ ያለ የፖለቲካ መዋቅር እንመርጣለን ሲል በሁለተኛ ደረጃ ደግሞ ሃብት ማፍራትም ሆነ ሌላ ክንዋኔ ጥሩ የሚሆነዉ በህብረተሰቡ ዉስጥ ያሉትን የዝቅተኛ መደብ አባላት የኑሮ ሁኔታ እስካሻሻለ ድረስ መሆኑን እናረጋግጣለን ይላል።

ድዎርኪን ደግሞ በበኩሉ መጀመሪያ ለህብረተሰቡ አባላት ሁሉ መነሻ  ወረት በጨረታ መከፋፈል አለበት፡ ወዲያዉ አስከትሎ ደግሞ ሁሉም ዜጋ ኢንሹራንስ ይገዛል። ማለትም መነሻ ወረት ቢኖር እንኳን ለምሳሌ አንድ ሰዉ ድኩማን ከሆነ ያንን ወረት በህክምና ጨርሶ እንደገና ደሃ የመሆን እድሉ ሰፊ ስለሆነ፤ ኢንሹራንስ ከተገባ ግን ይህን መጥፎ እጣ ለመቋቋም ይቻላል በሚል ነዉ። እነዚህን መላምታዊ ንድፎች በማንተራስ ሰዉ ኢጋጣሚዉን ሲያገኝ ፍትህ የተመላበት ስር  እንደሚመርጥ በማሳየት አብዛኞቹ ፈላስፎች ከመላምት ወጥተዉ በተጨባጭ ህብረተሰብ እንዴት እኩልነትንና ፍትህን ሊያነግስ ይችላል? በሚለዉ ተፋላስፈዋል። ምንም እንኳን ከሮበርት ኖዚክ በስተቀር አብዛኞቹ ተመሳሳይና ተወራራሽ ሃሳቦችን ቢሰነዝሩም፤ በዚህ ጽሃፊ አስተያየት የሚጋሩትን በጋራ ከማየት ይልቅ ልዩነቶቻቸዉን አጋንነዉ የሚያዩ ይመስላሉ። ሁሉም እየሰፋ የሚሄደዉን የሃብታምና የደሃ ልዩነት ይቃወማሉ፤ ሳንደል ለምሳሌ የጋራ ዜግነት ስሜትና ለሁሉም የሚመች ስርአትን ተስማሚነት ያሰምርበታል፤ አማርትያ ሴን ደግሞ ዜጎች ህይወታቸዉን ለመምራት የሚያስፈልጋቸዉን ቁሳዊና መንፈሳዊ ፍላጎቶች እንዲያገኑ ህብረተሰቡ ማስቻል አለበት ይላል።

ምናልባት ከሁሉም በተሻለ ሁኔታ ለአንድ ህብረተሰብ ደልዳላነትና ፍትህም ሰርጾ በህብረተሰቡ እንዲኖር በሰፊዉ ያተተዉ ጆን ራዉልስ ነዉ። ጆን ራዉልስ የመጀመሪያና ዝነኛ መጽሃፉን በጻፈበት በ 1970ዎቹ መጀመሪያ ላይ፤ በዚያን ወቅት አስተማማኝና የፍትህን ጥያቄ ላንዴና ለመጨረሻ መልሷል የተባለለት ማርክሲዝም ሌኒኒዝም በምሁራን ዘንድ ተቀባይነቱ በጣም ዝቅ እያለ የሄደበት፤ ህብረተሰባዊ ፍትህ ከማምጣት ይልቅ በሚዘገ ህብረተሰባዊ እልቂት እንዳደረሰ ማስረጃዎች የሚጠቀሱበት ጊዜ ላይ ነበር። ጆን ራዉልስ ማርክሲዝምን ለማሻሻል አልሞከረም። መሰረቱ ያደረገዉ የአማኑኤል ካንትን ፍልስፍና የሰዉ ልጅ ሙብት በምንም ሁኔታ መገሰስ የለበትም፤ ሰዉ ሁሌም ክቡር ነዉ ከሚለዉ መሰረታዊ ሃቅ ተነስቶ ነዉ። ከዚህም በመነሳት መሰረታዊ እሴቶች (primary goods) የሚላቸዉን እንደ ነጻነትና የስራና የትምህርት እድል፤ ገቢና ሃብት እንዲሁም አንድ ሰዉ ለራሱ "ክብሬ" ብሎ ለሚያምነዉ መሰረት የሚሆኑት ነገሮች ሁሉ ህብረተሰቡ ዉስጥ በእኩል መከፋፈል እንዳለባቸዉ አስተማረ። እኩልነትና ነጻነትን በጋራ አጣምሮ ታራቂነት ያላቸዉ እንጂ ጸበኞች እንዳልሆኑ አሳየ።

ባንጻሩ ሮበርት ኖዚክ የተባለዉ ፈላስፋ (ራዉልስም ኖዚክም ከሞቱ ወደሁለት አስርታት አካባቢ ሆኗል) ነጻነትና እኩልነት ተቃርኖ እንዳላቸዉና ነጻነት (liberty) ቀዳማይ እንደሆነች በታወቀዉ መጽሃፉ "ስርአተ አልበኝነት፤ መንግስትና ተምኔት" በተባለዉ አስተማረ። ባጭሩ ኖዚክ የሚለዉ እንደዚህ ነዉ።  አንድ ግለሰብ ሃብቱን ያለማስነካት ሙብቱ ክቡር ሙብት ነዉ (አማኑኤል ካንት የማይገሰስ የሰዉ ሙብት ብሎ ከሚያስተምረዉ በእጅጉ እንደሚለይ አንባቢ ያስተዉለዉ)። ይህ የሰዉየዉ ነጻነት ነዉ። በፈቃዱ ሰዉየዉ ከሃብቱ ቀንሶ ካላከፈለ በስተቀር መንግስትም ሆነ ሌላ በግዴታ የሰዉየዉን ሃብት ለማህበረሰቡ ጥቅም በሚል ሰንካላ ምክንያት ሊወስድ ፈጽሞ አይቻለዉም ነዉ። በኖዚክ ፍልስፍና የመንግስት ሚና በጣም ትንሽና ጠባብ ናት። ወንጀለኛን ከማሰርና ኮንትራት መፈጸሙን ከማረጋገጥ የዘለለ አይደለም። ይህን ፍልስፍና የሚጋሩና ያስተማሩ የታወቁ ኢኮኖሚስቶች እነ ፍሬዴሪክ ሃየክ፤ ሚልተን ፍሪድማንን የመሳሰሉ ይገኙባቸዋል። ተከታዮቻቸዉ በጋራ የሚጋሩት መንግስት ግብር የመሰብሰብ ሚና የለዉም ብሎ መካድ፤ መንግስት በሰናየ ተግባር መሳተፍና የሃብታሞችን ገንዘብ በመዉሰድ ለድሆች ማከፋፈል የለበትም የሚሉትን ያካትታል። አንዳንድ ልዩነቶች በመካከላቸዉ ቢኖርም ወግ አጥባቂ የሚባሉትን የምእራብ አገር  ፖለቲከኞች በጅምላ የሚይይዝ ሲሆን፤ ከመካከላቸዉ ደግሞ ጦርነትንና የዉጭ ጣልቃገብነትን ጨምሮ የሚቃወሙ "libertarian" የሚባሉ ንኡስ ክፍሎች አሉ።

ከመካከላቸዉ ዉስጥ ለምሳሌ ሃሪ ፍራንክፈርት የሚባለዉ ደፋር "ደሃ በድህነቱ ሊደሰት ይችላል። ያለኝ (ወይም የሌለኝ) እሱዉ ነዉ ወሰኔ፤ ሌላ አልፈልግም ሊል ይችላል። ስለዚህ ይህን ሙብቱን እናክብርለት" ብሎ ይሟገታል።

የሰዉ ልጅ ክቡር ነዉ የሚለዉን ለሚቀበሉ ክቡርነቱን ለማረጋገጥና በተግባር ለመተርጎም የሚያስፈልገዉን ይተነትናሉ። ሰዉ እየተራበ፤ እርጉዝ በዉስጧ ላለው ታዳጊ ህጻን በቂ ምግብ ሳታገኝ እየቀረች፤ አንዲት ሴት በነጻ የምታስበዉን ለመናገር ስትሞክር ወደ እስር ቤት እየተወረወረች፤ ወዘተ "ሰዉ ክቡር ነዉ" የሚለዉ በተግባር ሊፈጸም አይችልም። አይን ያወጡ ወግ አጥባቂዎችም ሆኑ፤ ስልጣንና ሃብት ጋፋፊ አምባገነኖች፤ የሰዉን ክቡርነትና እኩልነት በተግባር ማረጋገጥ አይቻላቸዉም። የፊተኞቹ ህጋዊም ይሁን በህገ ወጥ መንገድ ያካበቱት ሃብት "ተፍጥሯዊ" መብታቸዉ እንደሆነ ስለሚያዩት ይንከባከቡለታል፤ተለዋጭ አሳብ ሲቀርብ ይዋጉታል። የኋለኞቹ አንዳንዴ የአዞ እምባ በማፍሰስ የህዝብ ሞግዚት ነን በማለት ባንድ ጎን ሃብት እያጋበሱ፤በሌላ ጎን "ለተራዉም ህዝብ" የሚቻለነን እያደረግን ነዉ እያሉ ይምላሉ፤ይገዘታሉ። ተራዉ ህዝብ ግን እኔ የራሴን ጉዳይ ማስከበር እችላለሁ ብሎ ሲንቀሳቀስ "እኔ ካልኩህ ዉጭ አይቻልም" በሚል የሚያደርሱት ስቃይ ገሃነማዊ ነዉ።

፪

በዛሬይቱ ኢትዮጵያ የዜጎች ሰብአዊና ዴሞክራሲያዊ መብቶች ብቻ ሳይሆኑ የተሸበቡት፤ የድሆችም ብዛት ከአመት ወደ አመት እያሻቀበ እያደገ ነዉ። ዛሬ ኢትዮጵያዊ ዜጋ "መብቴ ተከብሯል፤ የደህነነት ስሜት ይሰማኛል፤ የወደፊቱም ኑሮየ ጥሩ እንደሚሆን ተስፋ አለኝ" ሊል እንደማይችል የታወቀ ነዉ። መንግስት ራሱ የዚህ ስጋት ምንጭ ነዉ። የነጻ ምርጫና የተለያዩ ሃሳቦች በሰላማዊ መንገድ የሚፋጩበት የዴሞክራሲ መሰረቶች በኢትዮጵያ ተንሸዋረዋል። ከመንግስት የተለየ ሃሳብ ወይም ፖሊሲ ተጻራሪ ሃሣብ ማቅረብ ፈጽሞ አይታሰብም። ከቀረበም ቅጣቱና የሚያስከፍለዉ ዋጋ እጅግ ዉድ ነዉ። ይህን ዉድ ዋጋ እየከፈሉ ካሉ ጀግኖቻችን በቅርቡ የታሰረዉ ደግሞ እዉቁ ጽሃፊ ተመስገን ደሳለኝ ነዉ። (ከክርስቶስ ልደት 500 አመት በፊት፤ የግሪክ ዴሞክራሲ ከአቴናና ከሌሎች የግሪክ የከተማ መንግስታት አልፎ ወደ አጎራባች ስልጣኔዎች ደርሶ ነበር። የነካቸዉም የግብጽን፤የፐርሽያንና የህንድን ሰፋፊ ግዛቶች ነበር። ሆኖም ከብዙ መቶ አመቶች በኋላ ወደተነሳዉ የኛዉ ገናና የአክሱም አገዛዝ አልደረሰም ነበር። ምናልባት የዴሞክራሲ ሽዉታ አክሱም ቢደርስ ኖሮ እኛም ዛሬ እንደ አዉሮጳ ዴሞክራሲ የደረጀበት አገር ለመሆን እድል ነበረን። ሆኖም የዚህን ተምኔታዊ ንግርት ታሪክ ለሌላ ቀን እንተወዋለን።)

ያለ አማራጭ አሳቦች ፍጭት፤ ግድብ ሳይደረገበት ለዜጎች የሚቀርብ የዜና ፈሰስ በሌለባት ኢትዮጵያ ላለፉት 20 አመታት በላይ ዴሞክራሲ የጌጥ እቃና ለዉጭ ዜጎች እይታ ብቻ ተንሳፍፋ የምትታይ ግኡዝ አካል ሆናለች። ከማስረጃዎቹ ሁሉ ደግሞ አሳፋሪዉ በ 2002 ምርጫ ገዥዉ ፓርቲ 99.6% ብሎ ማወጁ ነዉ።

ይህ ሁሉ ዉሰብስብ በሚታይበት አገር ነዉ በሃብታምና በድሃ መካከል ያለዉ የኑሮና የሃብት ልዩነት እየሰፋ የሚሄደዉ። እንደ 1966ና 1977 ኢ.ም የጠና ረሃብ አገሪቱ ላይ ባይመጣም፤ በርካታ ሚሊዮን ዜጎች በቂ ምግብ አያገኙም። ረሀብ በቀላሉ ሊያጠቃቸዉ ከሚችሉ 10 አገሮች አንደኛዋ ኢትዮጵያ እንደሆነች ብዙ ጠበብቶች ይስማማሉ። 30 ሚሊዮን የሚገመት ህዝብ በቀን ካንድ ጊዜ በላይ ለመብላት መቻሉ ያጠራጥራል። በዚህ ላይ የዋጋ ግሽበት በየጊዜዉ ሲከሰት ድሆችን ክፉኛ እንደሚደቁስ እንደ ሰይድ ሃሰን የመሳሰሉ ኢኮኖሚስቶች ደጋግመዉ አዉስተዋል። የአለም ባንክ እየከፈለ የሚያስተዳድረዉ የኑሮ ድጎማ (safety net) ባይኖር ኑሮ የረሃብተኛዉ ቁጥር በ እጅጉ ከፍ ይል ነበር። ከ 5-8 ሚሊዮን ህዝብ በዚህ የዉጭ ርዳታና ድጋፍ ተማምኖ የሚኖር ነዉ።

ይህ ዳረጎት በገጠር ድህነትን ለመቀነስ አስተዋጽኦ ቢያደርግም፤ በ ኢትዮጵያ የድሆች ቁጥር በየጊዜዉ ማደጉን አላቋረጠም። እንደ ጋርድያን የመሳሰሉ የዉጭ ጋዜጦች፤ መንግስት ያስፋፋዉን የጤና መዋቅርና የተወለዱ ህጻናት ሞትን በመቀነስ ያስመዘገበዉን ድል ከራሱ ከመንግስት ያገኙትን መረጃ ፤ መንግስትም ለለጋሽ አገሮችና አለም አቀፍ ተቋማት ያስተላለፈዉን መረጃ በማጣቀስ አዎንታዊ ዘገባዎችን ያቀርባሉ። መንግስት ደግሞ አሃዞችንና ቁጥሮችን በሚጠቅመዉ መንገድ እንደሚያዘጋጅና እንደሚከልስ ይታማል። ይህም ሆኖ ግን ሁሉ ነገር ደግሞ በአዎንታዊ መልክ ብቻ የሚታይ አልሆነም። ኤሚ ዎልተርስ የተባለች የብሄራዊ ህዝባዊ ሬዲዮ (NPR) ዘጋቢ በነሃሴ 14 ፤ 2014 ዘገባዋ  ከታወቁት የአገሪቱ ሆስፒታሎች አንዱ ስለሆነዉ የአዲስ አበባዉ ጥቁር አንበሳ ሆስፒታል ዘግናኝ ዘገባ አቅርባለች። የንጽህና ጉድለት፤ የ እቃዎች አለመሟላት፤ የመብራት መቋረጥ፤ የበሽተኞች ተደራርቦ ወለሎቹ ላይ መተኛትና በህጻናት ክፍል ደግሞ ባንድ አልጋ 3 ማስተኛትን የመሳሰሉ እንከኖችን ጠቅሳለች። ይህ እንግዴህ የከተማዋ ድሆች የጤና እንክብካቤ ያገኙበታል ተብሎ የተቋቋመ ሆስፒታል ነዉ። ሃብታሞቹማ መች አማራጭ አጥተዉ? ከንጹህ የግል ሆስፒታሎች እስከ ዉጭ አገር ሆስፒታሎች ድረስ የነሱ ተንከባካቢዎች ናቸዉ።

በዚያዉ በነሃሴ ወር ደግሞ ካሮላይን ኖዉልስ የተባለች የጋርድያን ጋዜጣ ባልደረባ ቆሼ በሚባለዉ ታላቁ የከተማዋ የቆሻሻ መጣያ ኑሮአቸዉን ባደረጉ ከ 200 እስከ 300 ስለሚደርሱ ዜጎቻችን አሳዛኝ ኑሮ ዘግባለች (ስእሎቹን ይመልከቱ)። ከዉሾች፤ ከፍየሎችና ከአሞሮች ጋር እየተሻሙ ቀኑን ሙሉ ጎብጠዉ በረጅም ዘንግ ቆሻሻ እያገላበጡ የሚሸጥ፤ የሚለወጥና የሚበላ ሲፈልጉ ይዉላሉ። ግፊያዉ አያድርስ ነዉ። ሽታዉ አያስቀርብም። በቦሌ ክፍለ ከተማ ከሚኖሩ ሃብታሞች ቤት የሚመጣዉ ቆሻሻና የኢትዮጵያ አየር መንገድ የሚጥለዉ የምግብ ትርፍራፊ ዋነኞቹ ተፈላጊ ናቸዉ። አልፎ አልፎ ደግሞ በሽሚያ ቅድሚያ ለማግኘት ከቆሻሻ መኪናዉ መድፊያ ላይ የሚሳፈሩ ጎልማሶች መካከል ቆሻሻ በሚያደቀዉ ሞተር እየተያዙ ይገደላሉ።

እነዚህ ዜጎች የመጨረሻዉ እርከን ላይ ይገኙ እንጂ አብዛኛዉ በከተማዋ ዉስጥ የሚኖሩ ዜጎችም ብዙ ከቆሼ ነዋሪዎች የተሻለ ኑሮ የላቸዉም። እጅን መታጠብ የሚባለዉ ግብረሰናይ ድርጅት እንደሚለዉ ከ 10 ቤተሰብ 9ኙ የጉድጓድ ሰገራ ቤት ይጠቀማሉ። የ35 ቤተሰቦች ባንድ የጉድጓድ ሰገራ ቤት መጠቀም የተለመደ ነዉ። የራሳቸዉ የጉድጓድ ሰገራ ቤት ያላቸዉ ከ 25 ቤተሰቦች አንድ ቤተሰብ ብቻ ነዉ። የሽታዉ ክፋት፤ የንጽህና ጉድለት ለተላላፊ በሽታዎችና ለተቅማጥ ኗሪዎችን ይዳርጋል። 35ቱ ቤተሰቦች በወር 1500 ብር እየከፈሉ ሰገራዉ እንዲመጠጥ ያደርጋሉ። ይህንኑ ገንዘብ ለማሟላትም ለዉጭ ተጠቃሚዎች 1 ብር ያስከፍላሉ። በከተማይቱ ዘመናዊ የሽንት ቤት ቱቦ አገልግሎት ያላቸዉ ኗሪዎች 2% ብቻ ናቸዉ። አዲስ አበባ ዉስጥ ንጹህ የቧምቧ ወሃ ተጠቃሚዎች ብዛት 64% ነዉ።

ሃብታሞችስ እንዴት ይቀናጣሉ?

"ደሞክራሲያዊና ሁለንተናዊ ልማት በኢትዮጵያ" በሚለዉ መጽሃፉ ብርሃኑ ነጋ አንድ ገጠመኙን ይተርካል። ከሌሎች ሰዎች ጋር ሼራተን አዲስ በተዘጋጀ የዉይይት መድረክ ንግግር ለማድረግ ሄዶ፤ ንግግሩን ከጨረሰ ብኋላ አንድ የሚያዉቀዉ ነጋዴ "ልጋብዝህ ብሎ" እዚያዉ ሸራተን ወደ መጠጥ ክፍሉ ይወስድዋል። ከዚያም አስተናጋጁን ቀዝቃዛ ያገር ዉስጥ ቢራ እንዲሰጠዉ ብርሃኑ ይጠይቃል። ጋባዡም "ቢራ አትጠጣም፤ ያንን መጠጥ አምጣለት" ይለዋል ለአስተናጋጁ። ጠጣ ፤ አልጠጣም ከቢራ በስተቀር ብለዉ ከተከራከሩ በኋላ ብርሃኑ አስተናጋጁን "ምን አይነት መጠጥ ነዉ ጠጣ የሚለኝ?" ብሎ ሲጠይቀዉ አስተናጋጁ ጠርሙሱን እያሳየ ልዩ ኮኛክና በመለኪያ 1500 ብር የሚያስከፍል እንደሆነ ይነግረዋል። ብርሃኑም በድንጋጤ "አገሪቱ በዚህ አመት ያመረተችዉ ጠቅላላዉ ምርት እኩል ለህዝቦቿ ቢከፋፈል እያንዳንዳችን ከ 1500 ብር በታች እንደሚደርሰን ታዉቃለህን? ይህ የመለኪያ ኮኛክ ዋጋ እኮ ያንድ መሃከለኛ ኢትዮጵያዊ የአመት ገቢ ነዉ" ብሎ ቀዝቃዛ ቢራዉንም ሳይጠጣ ከጋባዡ እንደተለያየ ይነግረናል። ዉስጥ አዋቂዎች እንደሚናገሩት ሸራተን ዉስጥ 22 የቮድካ አይነትና 31 የኮኛክ አይነት እንደሚሸጥ ይናገራሉ።

የኢህአደግ የዉጭ ደጋፊዎች መንግስት ድህነትን እንዲቀረፍፍና ሙስናን እንዲዋጋ አበክረዉ ከመምከር ይልቅ፤ ያገሪቱን እድገትና መሻሻል በጥሬ ቁጥሮች ብቻ ይመዝናሉ። አንዱ የእድገት መለኪያቸዉ ደግሞ በየአመቱ ስንት ሚሊየነሮች አገሪቱ እንደፈጠረች ነዉ። ዌልዝ ዶት ኮም የሚባለዉ ድረገጽ አገሪቱ በ 2007-2013 አመታት መካከል ከአፍሪካ አገሮች ሁሉ በላቀ መልኩ የፈጠረቻቸዉ ሚሊየነሮች እድገት 108% እንደሆነ ይነግረናል። በ 2007 ኢ.ም. 1300 ሚሊየነሮች የነበራት ኢትዮጵያ በ 2013 ቁጥራቸዉን ወደ 2700 አሳድጋለች። በዚሁ ከቀጠለ ዘንድሮ የሚሊየነሮቻችን ብዛት ወደ 3000 ይሆናል ማለት ነዉ። ይህ ቁጥር ቱባ ቱባ የመንግስት ባለስልጣን ሌቦችን ሁሉ የሚጨምር እንደሆነ መገመት አያዳግትም። ለነሱ ፌሽታና አመት በአል ሲሆን ለ 30 ሚሊየን ረሃብተኞች ግን ሰቆቃ ነዉ።

ፍትህ የመላባትና የዜጎቿ ሙብት የተከበረበት ኢትዮጵያ እንድትፈጠር 40 አመት በፊት አንድ አብዮተኛ ትዉልድ ህይወቱን ለመስዋ እትነት፤ የሰዉነት ክፍሎቹን ለስቃይና ለእስር መስዋእት አድርጓል። ያለመታደል ሆኖ ዛሬ በዘመነ ኢህአዴግ ወደኋላ ጉዞዉ በተቀላጠፈ ፍጥነት እየቀጠለ ነዉ። በጣም የሚያስገርመዉ ደግሞ ለድሃዉ ለትግራይ ህዝብ ሙብት ለመታገል ወደ ዱር ወጥተን ነበር የሚሉ አንዳንድ የህውሃት አባላት ዛሬ በሙስና ተነክረዉ በሚያማምሩ ቪላ ቤቶቻቸዉ ራሳቸዉን ከተራዉ ህዝብ ለይተዉ በመቀሌ ምርጥ ቦታዎችና በአዲስ አበባም እንደ ቦሌ በመሳሰሉ ልዩ ቦታዎች ሲኖሩ ነዉ። ከመካከላቸዉ ጥቂቶቹ የትናንት ቦታቸዉን ረስተዉ በጥጋብ ብዛት ለድሆች ያላቸዉ ንቀት የት የሌሌ ነዉ። ታዋቂዉ የህሊናና የፖለቲካ እስረኛ አንዱ አለም አራጌ በጻፈው መጽሃፍ "ያልተሄደበት መንገድ" አንድ አስገራሚ ኩነት ይነግረናል። "በማእከላዊ ምርመራ ወቅት የባንክ ቡኬን ካዩ በኋላ ደጋግመዉ የሚሰድቡኝ "ደሃ፤ የድሃ ልጅ" የሚል ነበር፤ በተለይም የህወሃት አባሉ። እንደነሱ ዘርፌ አለማካበቴ ምቾት አልሰጣቸዉም " ።(ገጽ 105)

ምን ይሉታል ይህን ቅሌት?

አገዛዙ ሚሊዮን ዜጎችን ወደታች እርከን በመጣል ላይ የተመሰረት ብቻ ሳይሆን ወደላይ የወጡት ደግሞ እንዳሻቸዉ የሚዘርፉበት ስርአት ሆኗል። ኤርምያስ ከበደ ስለዚህ ሙስና በሰፊዉ "የመለስ ትሩፋቶች" በሚለዉ መጽሃፉ ይተርካል። ከነዚህ መካከል አንዱን ብቻ መጥቀሱ ለምሳሌነት ይበቃል። የዶ/ር ቶውፊቅ አብዱላሂ ሙስና ለከት የለዉም። በሃሪሪነቱ ከመንግስት ፓርቲ ጋር ወግኖ ያለምንም ማእቀብ የሚሰራዉ ግፍ ብዙ እህቶቻችንና እናቶቻችንን ያስለቀሰ ነዉ። ወደ መካከለኛዉ ምስራቅ ለአሽከርነት የሚሰደዱ ሴቶቻችንን ለጤንነት ማስረጃ ምርመራ እያለ በነፍስ ወከፍ ከያንዳንዳቸዉ 1000 ብር ይበላል። ሲያሻዉ በዉሸት"ኤይድስ/ኤች አይ ቪ በሽታ አለብሽ" እያለ ለብዙ ሴቶች የሃሰት ማስረጃ ሰጥቷል። ተስፋ ያልቆረጡና ዉሸታምነቱን የጠረጠሩ ሴቶች ከሃቀኛ ዶ/ሮች ጤናኛ መሆናቸዉን የሚያረጋግጥ ማስረጃ አግኝተዋል። በዚህ ወንጀሉ ተቀጣ? እንኳን ሊቀጣ እንዲያዉም አልተሳካለትም እንጂ የኢትዮጵያ ስፓርት ፌዴሬሽን ፕሬዚደንት ለመሆን ተወዳድሮ ነበር (ገጽ 64)። ሌላዉ የሙስና አስረጂ ምሳሌ ደግሞ ከብርሃኑ ነጋ ጋር በኢትዮጵያ የኢኮኖሚ ባለሙያዎች ማህበር ባልደረባዉ የነበረ ሰዉ ነዉ። ብርሃኑ እንደሚለዉ "አንድ የማህበራችን አባል ከቀረቡለት የተለያዩ የስራ አማራጮች ዉስጥ የጸረ-ሙስና ኮሚሽንና ያዲስ አበባ ምክር ቤት እንደነበሩ ይገልጽልናል። በግልጽ የኋለኛዉን መርጦ የገባበት ምክንያት ይህዉ "ይበላበታል" መስፈርት መሆኑን ሳይደብቅ፤ ያለማፈር ነበር ያጫወተኝ" (ገጽ 192)።

ተከታታይ ትዉልድ በድህነት አረንቋ ዉስጥ በዘለአለማዊነት ተጠምዶ ድህነትን ከወላጆቹ እንዳይወርስ ታላቁ ፍቱን መድሃኒት የትምህርት እድልን ማስፋፋት ነዉ። ሰዉ በሙያዉ፤ በትምህርቱና በባህሪዉ ብቻ ለስራና ለ እድገት በሚታጭበት ህብረተሰብ፤ የድሃ ልጅ ደሃ ሆኖ የሚቀጥልበት እድል በጣም ጠባብ ነዉ። በም እራብ አገሮች ይህ ሃቅ በሰፊዉ ይታያል። ሆኖም ከነሱ መካከል አንዳንዶቹ የገንዘብ ሃይል፤ የዉርስ ገንዘብና "ማንን ታዉቃለህ?" የዘመድ ንኪኪ ተግዳሮት እየፈጠረባቸዉ ነዉ። ቢሆንም የድህነትን አዟሪት ለመስበር ትምህርት ያለዉ ቦታ በምንም አይናወጽም። የዛሬይቱ ኢትዮጵያስ የትምህርት አይነት፤ ጥራትና ድሆች ለትምህር ያላቸዉ ቀራቦት የድህነትን ቀንበር ለመስበር አጋዥ ነው ወይ? የሚለዉን በሚከተለዉ ክፍል እንመልከት።



የትምህርት ጥራት እየወረደ ከሄደ በግምባር ቀደም የሚጎዳዉ የድሃ ልጆችን ነዉ። ሃብታሞቹማ ሀብታም ሆነዉ ለመቀጠል  በገንዘብ ሃይልና በስልጣናቸዉ የተለያየ ምርጫ ይኖራቸዋል። የትምህርት ባለሙያዎች እንደሚናገሩት ከ 1-5 ባሉት አመታት መካከል ያሉ ህጻናት አእምሮአቸዉ የሚበለጽግበትና መሰረት የሚጣልበት ወቅት መሆኑን ነዉ።   ስለሆነም ጠበብቶች በነዚህ እድሜ ክልል ላሉ ህጻናት ትምህርትና እንክብካቤ ህብረ ተሰቡ አስፈላጊዉን ወጭ እንዲያደርግ ያሳስባሉ። በኢትዮጵያ ገና ሲጀመር ተፈጥሮ (ወይም ቸልተኛ መንግስት?) በተወሰኑት ላይ የመጀመሪያዉን ጨካኝ ዉሳኔ ታስተላልፍባቸዋለች። ከሚወለዱ 1000 ህጻናት ዉስጥ 68ቱ እድሜያቸዉ 5 አመት ሳይሞላ ከዚህ አለም በሞት ይለያሉ። ዛሬ ተሻሽሎ ነዉ እንጂ ከዛሬ ሃያ አመት በፊት ሟቾቹ 200 ያህል ነበሩ። ይህ ስሌት እንግዲህ መንግስት ለአለም አቀፍ ድርጅቶችና ለለጋሽ ድርጅቶች የሚሰጠዉን ቁጥር በመጠቀም ነዉ።

እነዚህ 68 ከ 1000 ሟች ህጻናት ባመዛኙ የድሃ ልጆች ለመሆናቸዉ ግልጽ ነዉ። ድሃ እናቶቻቸዉ በእርግዝና ጊዜ በቂ ምግብ፤ የተመጣጠነ ምግብና የጤና እንክብካቤ ለማግኘት ስለማይችሉ የወለዷቸዉ ልጆቻቸዉ 5ኛዉን ልደታቸዉን ሳያከብሩ ይሞታሉ። በተአምር ከተረፉት ዉስጥ ደግሞ ግማሾቹ ያህል የድሃ ልጆት በድህነት ምክንያት ትምህርት ቤት አይሄዱም። የሚበላ የለም፤ መጠጊያ የለም። እነዚህም ቢገኙም ለትምህርት የሚያስፈልጉ መሳሪያዎችን መግዛት አይችሉም። ይህ እንግዲህ ሁለተኛዉ አስዛኝ ምት ነዉ። አንዳንድ ጥናቶች እንደሚያሳዩት 5% የሚሆኑት የድሃ ልጆች ትምህርት ቤት በር ላይ ለመድረስ ይችላሉ። እነዚህም ብዙ መሳሪያ ና አገልግሎት የሌላቸዉ መዋእለ ህጻናትና ትምህርት ቤቶች ይሆናሉ። ገንዘብ ያላቸዉ ወላጆች ትምህርት ቤት አማርጠዉ፤ ልጆቻቸዉን በቂ ግልጋሎት ወደሚያገኙበት ጥግ ያስይዟቸዋል። ይህ እንግዲህ የድሃ ልጆችን የሚገጥም ሶስተኛ ምት ነዉ። ይህ እጣ በዚህ ደረጃ ብቻ አያቆምም። ልጆቹ በርትተዉ ትምህርት ከቀጠሉ እስከ መካከለኛና ሁለተኛ ደረጃ ትምህርት ድረስ ይከተላቸዋል። ትምህርት ሚኒስቴር እንደሚለዉ ግማሽ በግማሽ የሁለተኛ ደረጃ ተማሪዎች ትምህርታቸዉን አቋርጠዉ ስራ አጥ የሚሆኑ ናቸዉ።

አሳዛኙን የዛሬዉን የትምህርት ሁኔታ በተመለከተ አንዳንድ ተቆርቋሪ ዜጎች ሃገር ቤትም ዉጭም የሚገኙ ምሬታቸዉን፤ ስጋታቸዉንና ማሻሻያ ሃሳቦች የሚሏቸዉን አካፍለዋል። ከነዚህ መካከል እኔ ያነበብኳቸዉ ጽሃፍት፤ ካልአዩ አብርሃ፤ ቅዱስ ዮሃንስ፤ ሳምራዊት ህሩይ፤ አሰፋ በላቸዉ፤ የጉልጉል ድረገጽና ዋዜማ ፖድካስት ላይ ቃለመጠይቅ የሰጡት አብርሃም አለሙና እንዳልካቸዉ ሃይለሚካኤል ይገኙባቸዋል።

በተጠቃለለ መልኩ የሚሏቸዉ የሚከተሉት ናቸዉ።

1. ትምህርት የፖለቲካ መሳሪያ ሆኗል፤  ያገሪቱ መሪ የነበረዉ ራሱ መለስ  ፓርላማ ተብየዉ ፊት ቀርቦ የሱ ፓርቲ፤ ካንድ ሰዉ የትምህርት ብቃት ይበልጥ ለሱ ፓርቲ ያለዉን ታማኝነት ይበልጥ ዋጋ እንደሚሰጠዉ ሲናገር፤ አንድሞታዉ ቀላል አልነበረም። እንዳለዉም በንግግር ብቻ የቀረ አልነበረም። ያገሪቱ ፖሊሲ የሆነ ያህል ነዉ። የትምህርት ሹመት በፖለቲካ ታማኝነት ሚዛን ነዉ የሚለካዉ፤ ካድሬዎች አድራጊና ፈጣሪ ናቸዉ፤ አስተማሪዉን ያዝዛሉ፡ የፈተና ቀን ያስለዉጣሉ፤ የሚፈልጉትን ከፍተኛ የትምህርት ዉጤት ያገኛሉ። በፖለቲካ ታማኝነታቸዉ ምርጥ ስራ እንደሚያገኙ ስለሚያዉቁ ጥናትና ለትምህርት ክብር ሲያልፉም አይነኳቸዉም። የደሃ ልጆች ግን ሌላ ምርጫ ስለሌላቸዉ ከካድሬ በታች የትምህርት ዉጤት እያገኙ፤ ስራ ቢፈልጉ ገዥዉን ፓርቲ መጎናበስና ደጋፊ ወይም አባል መሆናቸዉ ግድ እንደሚል እያሰቡ የህሊና ቁስል ይደርስባቸዋል።
2. የዲስፕሊን ጉድለት፤ የትምህርቱ ስርአት ፍትህ የጎደለዉ በመሆኑ ፤ የትምህርት ቤት ስነ ስርአት ማክበርና ለህግጋት ተገዥ መሆን ባእድ እየሆኑ መጥተዋል። ከትምህርት ገበታ መቅረትና ለፈተና ቀን ብቻ መምጣት፤ ፈተናና የቤት ስራ ማጭበርበር፤ ትምህርት ቤት ግቢ ዉስጥ መደባደብ የተዘወተሩ ተግባሮች ሆነዋል።
3. የትምህርት ደረጃ ማሽቆልቆል፤  እጅግ አሳሳቢዉና ዉስብስቡ ችግር ይሄ ነዉ። በየቦታዉ ብቃት የሌላቸዉ ኮሌጆች በመከፈታቸዉ መሟያ አስተማሪ ለማግኘት ብቃት የሌላችዉን አንደኛ ዲግሪ ብቻ ያላቸዉን ማግብሰበስ የተለመደ ሆኗል። እነዚህ አስተማሪዎች ደግሞ ሁለተኛ ደረጃ ዲግሪ ለማግኘት የብቃት መለኪያ ፈተና የትም አገር እንደሚደረገዉ አይወስዱም። በትምህርት ሚኒስቴር ህግ መሰረት የኮሌጅ አስተማሪ ስለነበሩ ብቻ ሁለተኛ ዲግሪ ፕሮግራም መግባትና መመረቅ መብታቸዉ ነዉ። እኒህ ብቃት የሌላቸዉ መምህራን ደግሞ ብቃት የሌላቸዉን ተማሪዎች እያስተማሩ የቁልቁለት መንገዱን ተያይዘነዋል። ይህ እንግዲህ የገዥዉ ፓርቲ ከፍተኛ አባላት በግዥ ከዉጭና ከዉስጥ ከሚያካብቱት የዉሸት ዲግሪ በተጨማሪ ነዉ።የወረደውን የትምህርት ደረጃ በአብነት የሚያሳጣዉ የተማሪና ያስተማሪ የ እንግሊዝኛ እዉቀት ዉድቀት ነዉ። መንግስት 70/30 በሚል ፖሊሲ የሳይንስና

የሂሳብ ምሩቃንን ለማሳደግ ፖሊሲ አለኝ ቢልም፤ አንዳንድ ተቺዎች እንደሚሉት የሳይንስና የሂሳብ ትምህርት እንደ ኤይድስ በሽታ የሚፈራ ሆኗል። ብርሃኑ ነጋ፤ ፎረም ፎር ሶሽያል ስተዲስ የሚባል የምርምር ተቋም በ 2009 ኢ.ም. ያወጣዉን አሃዝ በመጽሃፉ ጠቅሶ፤ በ 2007 ኢ.ም. የሁለተኛ ደረጃን መልቀቂያ ፈተና ከወሰዱ ተማሪዎች ዉስጥ ያለፉት 7.6% ብቻ መሆናቸዉን፤ ይባስ ብሎ ደግሞ በሚቀጥለዉ አመት በ2008 3% ብቻ ማለፋቸዉ ትምህርት ለማሾቆልቆሉ ማስረጃ መሆኑን ያሳያል (ገጽ 172)

4. <u>ከጥራት ብዛት፤</u> በቁጥር ላይ ብቻ ተቀባይነትን ለማግኘት የሚደክም መንግስት፤ ስለጥራትና ስለ ትዉልድ የወደ ፊት ኑሮ ብዙ አይጨነቅም። ለጋሽና አጋዥ አገሮችም ይህንኑ ቁጥር እንደ በቀቀን እየደጋገሙ በመጥቀስ የሰጡት ርዳታ በበቂ ጥቅም ላይ እንደዋለ ራሳቸዉንና ግብር ከፋይ ህዝባቸዉን ለማሳመን ይጥራሉ። "ከዚህ በፊት ከነበሩት 4 ዩኒቨርሲቲዎች ወደሰላሳ በላይ ዛሬ አድጓል" የሚለዉ ተደጋግሞ ተሰምቷል። ሆኖም እነዚህ ከ 30 በላይ ተቋሞች ምን ይመስላሉ? ብሎ ይዞታቸዉን፤ የሚሰጡትን ትምህርት፤ የመምህራኑን ጥራት፤ ወዘተ በዝርዝር ተጨንቆ ያጠና ያለ አይመስልም። የተያዘዉ እንዲያዉ ደግሞ ደጋግሞ "ከ 30 በላይ ዩኒቨርሲቲ" የሚል መፈክር ማዉረድ ብቻ ይመስላል። ዜሮን በዜሮ በማባዛት፤ የትምህርት ሁኔታዉን ለማጥናት በሚል አማካሪዎችና የፓርቲ ደጋፊ ነጋዴዎች ከፍተኛ ገንዘብ ተከፍሏቸዉ አዉደ ጥናቶች የሚያዘጋጁበት፤ "ትምህርትን ለማሻሻል ቢደረጉ ጥሩ ነዉ" የሚባሉ ተመሳሳይ ሃሳቦች በየጊዜዉ የሚፈልቁባቸዉ ሆኖም የማይፈጽምባቸዉና ደማቅ መፈክሮች በጽሁፍ የሚሰቀሉባቸዉ የገንዘብ ብክነት የተለመደ ነዉ።

5. <u>ትምህርት እንደ አትራፊ ንግድ፤</u> የግል ኮሌጆችና የሙያ ተቋሞች፤ ብዙም ቁጥጥር የማይደረግባቸዉና ደረጃቸዉን ያልጠበቁ፤ ለተማሪዎቻቸዉ የማለፊያ ዉጤት ሁልጊዜ ካልሰጡ ንግዳቸዉ ትርፍ እንደማያገኝ ያሰሉ ትምህርትን መነገጃ ያደረጉ የዘመኑ ክስተቶች ናቸዉ።

6. <u>ጎጣዊ ትምህርት፤</u> የትምህርት ዋና አላማዉ ሙሉ ኢትዮጵያዊ ዜጋ ማፍራት ነዉ። ይህዉም የሚከናወነዉ ያገሩን መልክአ ምድር፤ ታሪክ፤ በጎ በጎና የጋራ ክንዋኔዎችንና ለዘመናት አብሮ ኗሪነትን መሰረት ያደረገ እዉቀት ማነጽን ነዉ። ትምህርትን ወደ አካባቢዎች ማዉረድና አስተዳደሩን በክፍለ አገር ደረጃ ማዛወር በጎና ለህዝብ ስልጣን የሚያጎናጽፍ ርምጃ ሊሆን ይችላል። በዚህ ሽፋን ትምህርትን ጎጣዊ ማድረግ ግን ኢትዮጵያዊነትን ይጎዳል። ዛሬ የሚታየዉ ባንድ ክልል ያሉ ኢትዮጵያዉያን ተማሪዎች ስለሌላ ክልል ተማሪዎች ብዙ የማያዉቁበት፤ ራሳቸዉን ልዩ አድርገዉ ተያያዥ ታሪካቸዉን የማይዘከሩበት፤ እንዲያዉም የሌሎች ክልል ኗሪዎችን በጠላትነት ሲበዛ፤ ሲያንስ ደግሞ በባይተዋርነትና በጥርጣሬ የሚያዩበት ስር አት ላይ እንገኛለን።

7. <u>የአካዴሚክ ነጻነት መጥፋት፤</u> ከፍተኛ የትምህርት ተቋማት በተለይ ተማሪዎቻቸዉና መምህራኖች በነጻ በሙያቸዉና በአገራቸዉ ጉዳይ የሚወያዩበት፤ የሚደራጁበት፤ የሚጽፉበትና የሚከራከሩባቸዉ ተቋማት መሆን ይገባቸዉ ነበር። ዛሬ የሚታየዉ ግን የካድሬ ስርአት ከደርግ ዘመን ጀምሮ ድሩን እንዳደራና ባስከፊ ሁኔታ እንደቀጠለ ነዉ።

8. <u>የሽምደዳ ትምህርት ዘይቤ፤</u> የትምህርት ስርአቱ በራስ አነሳሽነት ማሰብን ፤መመራመርን፤ መጠየቅንና የተለየ ሃሳብ ለማቅረብ አለማመንታትን አያበረታታም። የሰጡትን መልሶ በቁሙ መዉረድን ያበረታታል። ይህ ደግሞ ከትምህርትና ከእዉቀት ዋነኛ አላማ ጋር ይጋጫል። በሽምደዳና መልሶ በመዉረድ አዲስ ሃሳብና ግኝት አይገኝም።

9. <u>የትምህርት ቤቶችና መሳሪያዎች ብቃት ማነስ፤</u> ከሁሉም ከላይ ከተዘረዘሩት ህጸጾች ይህኛዉ ለማስተካከል ቀላሉ ነበር። ከ 30 ዩኒቨሪሲቲዎች በላይ የሰራ መንግስትና በርካታ ቢሊየኖች በርዳታ የሚያገኝ መንግስት የተማሪ ወንበሮችንና ጠረጴዛዎችን መጠገን ወይም አዲስ ማቅረብ ባላስቸገረዉ ነበር። አንዳንድ ትምህርት ቤቶች ግድግዳዉ ላይ የተቀባዉ ቀለም እየረገፈ ሲታይ፤ አንዳንዶቹ ጋ የኮረንቲ ሽቦዎች በመግጠሚያ መሰብሰብ ሲኖርባቸዉ አደጋ በሚፈጥሩበት ሁኔታ ተዝረክረከዉ መታየታቸዉ፤ በየጊዜዉ የሚቋረጠዉ መብራት ትምህርት እንዳያስተጓጉል ተተኪና ተጠባባቂ የሃይል ማመንጫዎች (ጀነረቶሮች) አለመኖር ወይም አለመስራት፤ ለዘመናዊ ትምህርት ምርምር ዋልታና ማገር የሆነዉ የኢንተርኔት አገልግሎት አለመሟላት አሳሳቢ ችግሮች ሆነዋል።

ራሱን ልማታዊ መንግስት ነኝ ብሎ የሚናገረዉ መንግስት ቢያንስ ቢያንስ ይህን ለማሳመን ሊወስዳቸዉ ከሚገቡት ርምጃዎች ከፊሉን እንኳን እየወሰደ አይደለም። ሌላዉ ይቅር። የፖለቲካ መብት መረጋገጥና የዜጎች መታሰር ማቆም፤ የታሰሩት መፈታት፤ ህዝቡ በነጻነት የሚፈቅደዉን መንግስት የመምረጥ መብት ምንም እንኳን ለነገ ይደሩ የማይባሉ ቢሆንም ልማታዊ ነኝ የሚል መንግስት ይህን እንኳን ለመፈጸም ቢያቅተዉ፤ በድሆችና በሃብታሞች መካከል ያለዉን ልዩነት ለማጥበብ ርምጃዎች ሲወስድ በጉልህ አይታይም። ሌላዉ ቀርቶ አብዛኛዉ ኢትዮጵያዊ ለኢትዮጵያ ትገባለች የሚላትን የአሰብ ወደብን እንኳን ህጋዊ በሆነ መንገድ ወደ ኢትዮጵያ መልሶ ለማምጣት ጭንቀትን አያሳይም። በአንጻሩ ጌታቸዉ በጋሻዉና ሌሎችም እንዳሳዩት ለጂቡቲ መንግስት በ አመት $745 ሚሊየን ይከፍላል። ዝርዝሩ ሲሰላ እያንዳንዱ የጂቡቲ ተወላጅ በቀን $4 . 3 ከ ኢትዮጵያዉያን በችሮታ መልክ ይሰጠዋል። ይህ እንግዴህ ከ 30 ሚሊየን ህዝብ በላይ በቀን ከ $1 በታች ገቢ ያለዉ ኢትዮጵያዊ በ ኢህ አደግ ችሮታ ራሱ እየተራበ ለጂቡቲ ህዝብ በፈቃደኝነት የሚያበረክተዉ ነዉ። ሌላም ህገወጥ ወጭ አለ። እስከ $12 ቢሊየን ያህል ያገሪቱ አንጡራ ሃብት ወደዉጭ መደበቂያ ባንኮች በህገወጥ መንገድ የመንግስት ባለስልጣኖች

እንዳሸሹ ተደጋግሞ ተዘግቧል። ጥቂት የታች ባለስልጣኖችን በማሰር በግማሽ ልብ ጸረ-ሙስና ርምጃ እወስዳለሁ ብሎ በማለት ሳይወሰን ከታች እስከ ላይ እዉነተኛ የጸረ-ሙስና መከላከል ፍትህ ላይ ቢሰማራ የሚሰበሰበዉ ገቢ ለድሆች መደጎሚያ ብዙ ይረዳ ነበር።

ከመካከላችን ዉስጥ የቆሼ ኗሪዎች ልጆች የወላጆቻቸዉ እጣ ፈንታ እንደማይደርስባቸዉና ከወላጆቻቸዉ የተሻለ ኑሮ እንደሚኖሩና ከድህነት አዟሪት ዉስጥ እንደሚወጡ የሚገምት ይኖር ይሆን? ይህ መንግስት በስልጣን ላይ አስካለ ድረስ ወይም በያዘዉ የስህተት ጎዳና እስከተጓዘ ድረስ ይህ የማይታሰብ ነዉ።

በሃብታምና በድሃ መካከል እየሰፋ የሚሄደዉን የኑሮና የሃብት ልዩነት ለማጥበብ ትግል ማድረግ የተቀደሰና ፍትሃዊ ትግል ነዉ። ችግሩ ያንድ ጎሳ ወይም ያንድ አካባቢ፤ ያንድ ጾታ ወይም ያንድ ሃይማኖት ስላልሆነ ተቆርቋሪ ኢትዮጵያዉያንን በኢትዮጵያዊነታቸዉ ብቻ በህብረት ለያሰባስብ የሚችል ፍትሃዊ የዜግነት ግዴታ የሚጠይቀዉ ትግል ነዉ።

ሕዳር 2007 ኢ.ም.